# ጬኸት ከምድረ ወልቃይት፤

5/07/2008

በጎንደር ክፍለ ሃገር በተለይም (በወልቃይት ጠገዴ, ጠለምት) እና በትግራይ ሕዝብ መካከል እስከ 1970ዎቹ መጨረሻ ድረስ ከነበረው ታሪካዊ አንድነት ባሻገር፡ በመፈቃቀድ የተመሰረቱ ግቢዎች የንግድ ልውውጦሽ በጋራ የተፈጥሮ ድንበር የሆነውን የተከዜ ወንዝ የመጠቀም ወዘተ.... የመሳሰሉ ጠንካራ ግንኙነቶች እንደነበሩት ይታወሳል።

በተልይም የተፈጥሮ ድርቅ በተደጋጋሚ በትግራይ ክፍለ ሃገር በተከሰቱባቸው ወቅቶች እጅግ በርካታ የሆነ ሕዝብ ወደ ጎንደር ክፍለ ሃገር (ወልቃይት ጠገዴ) በመሻገር የተፈጥሮ ርህራሄ ቸርነትንና ለጋሽነትን ተለይቶት ከማያውቀው ወገኑ ጋር በመቶየት ጊዝያዊ ችግሮችን እንዲወጣ፤ እዲጠናከር በማገዝና ከተጠናከረ በኋላም የሥራ እድል በማመቻቸት የመልሶ ማቋቋሚያ ገንዝብ ይዞ እንዲመለስ ሲደረግ ቆይቷል።

በወልቃይትና ጠገዴ ለም መሬቶች (መዘጋ፤ ሁመራ፤ ዳንሻ፤ ወዘተ...) የልማት እንቅስቃሴዎች ከተጀመረም በኋላ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ የትግራይ ተወላጆች ወደነዚህ አካባቢዎች በመምጣት ወቅታዊ የሥራ ዕድል እንዲያገኙ ሲደረግ፤ ለመኖር የወሰኑት ቤተሰቦችም ሕዝቡ እጁን ዘርግቶ በመቀበል ትብብር ሲያደርግላቸው እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። ይህን እድል በመጠቀምም የተሻለ ኑሮ ከመኖር አልፎ እስከ ከፍተኛ ሀብት ማካበት ድረስ የደረሱ የትግራይ ሰዎች እንደነበሩም ይታወቃል። ለምሳሌ ከብዙዎቹ ባለሃብቶች ጥቂቶቹን ብንጠቅስ፤

1ኛ.አቶ ተስፋይ አድዋ (የውጭ ጉዳይ ሚኒስተር ስዩም መስፍን አጎት፡ ኋላ ከወያኔ ጋር በማበር ለሀብት ያበቃቸውንና ያመናቸውን ሕዝብ ክደው እንደእባብ ያስቀጠቀጡት፡)

2ኛ.አቶ ታፈረ አድዋ 3ኛ.አቶ ኪሮስ አለማዮሁ 4ኛ.አባ መሰለ

5ኛ.አቶ ኀይለስላሴ

6ኛ.አቶ መሃመድ ያሲን

7ኛ. አቶ ጣሀር ፍትዊ፡ የመሳሰሉ ይገኙበታል።

ባጪሩ የጎንደር መሬት (ወልቃይት ጠገዴ) እስከ 1970ዎቹ ድረስ ለትግራይ ብቻ ሳይሆን ለመላው ኢትዮጵያዊ በሩን ከፍቶ ያስተናገደ እንደነበር ያኔ በተለያዩ ኢትዮጵያውያን ቀለም አሸብርቃና አብባ የነበረችው ሁመራ ከተማ ምስክር ነች። ታድያ ሀቁ ይህ ሆኖ ሳለ የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጪ ግንባር (ወያኔ) ታላቋ የትግራይ ሪፓብሊክ ለመመሥረት ከነበራትና ካላት እጅግ ጠባብ ምኞት በመነሳት የወደፊቷ የትግራይ ሪፓብሊክ ሲኬታማ እንዲሆን ጠቃሚ የምትላቸውን ለም መሬቶችና መውጫ በር ተሟሙቶ መያዝ አማራጭ የሌለው መንገድ እንደሆነ በማበከር፡ በ1970ዎቹ መጨረሻ ላይ የተፈጥሮ ድንበር የሆነውን የተከዜ ወንዝ በመሻገር የጎንደር መሬቶችን ወልቃይት ጠገዴና ጠለምት በጉልበት ያዘች። ወያኔ ልትደርስበት ያቀደችውን አገር የመናድና የመሸጥ፤ ወገንን የመከፋፈል፤ ህልምና ቅጅት አስቀድሞ የተረዳው የወልቃይት ጠገዴና ጠለምት ሕዝብ፤ ከጥዋት

ጀምሮ በወያኔ ላይ መሳሪያውን በማንሳት እጅግ ከፍተኛ ተጋድሎ አድርጓል እያደረገም ይገኛል።
የዚህ አካባቢ ሕዝብ ያደረገው መራራ ትግል ለወያኔ የእግር እሳት እንደሆነ በማመን፤ ወያኔ ቂሟን ለመበቀል ጊዜና ሰዓት ስትጠብቅ ቆይታ፤ መንግስታዊ ኀይሏን አደራጅታ ከሂትለር ባላነሰ የጥፋት ራዕይ በመመራት በወልቃይትና ጠገዴ ተወላጅ ኢትዮጵያን ላይ ይህ ነው የማይባል የጥፋት ዘመቻ እያካሄደች ነው።

ወያኔ በዚህ ብቻ አላቆመችም ወገንን አጥፍቶ በሌላ ወገን የመተካት ዘመቻ እውን ለማድረግ ለምሳሌ ያህል ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን በደሎች ፈጽማለች።

1. አንድ ወገን (የወልቃይትና ጠገዴ) ሕዝብ ለማጥፋት፤

ሀ) በብዙ ሺ የሚቆጠሩ አገር ወዳድ ግለሰቦች አዛውንቶች ጭምር እስከነሕይወታቸው በወያኔ ሠው ሰራሽ ጉድጓድ (ባዶ ስድስት) እስር ቤት በመጣል በታሰሩበት ጉድጓድ ውስጥ እየተጸዳዱ የፀሓይ ብርሃን ሳያዩ ሰውነታቸው ተልቶና ሚሽሾ እንዲያልቁ፤

ለ) በሆነ ባልሆነ ምክንያት እጅግ ከፍተኛ የገንዝብ ቅጣት በመበየን ያለ የሌለውን ንብረቱን አሟጦ ዘርፎ በድህነት ማቆ ውስጥ እንዲገባ፤

ሐ) በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ነዋሪዎች ቀያቸውን ጥለው እንዲሰደዱ፤

መ) ያለሙትን የርሻ መሬታቸውን ተንጠቆ ለርሻ ብዙ በማያመቹ ደጋማ ቦታዎች እንዲሰፍሩ፤

ሠ) በባህሉና በቋንቋው እንዲያፍር፤ ወኔውም እንዲሟሽሽ፤ በሁለንተናዊ መልኩ ከሰብእና ውጭ እንዲሆን ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል።

2. በሌላ ወገን ለመተካት

ሀ) የወልቃይት ጠገዴ ተወላጅ የውጭ ወራሪ እየተከላከለ ሃሩርና ቁርን በሺታውን ተቋቁሞ ያቀናውንና ያለማውን መሬቱ (መዘጋ ወልቃይት፤ አዲጎሹ፤ ሁመራ፤ ዳንሻ፤ ወዘተ...) በግድ በማስለቀቅና በማፈናቀል በብዙ መቶ ሺ የሚቆጠሩ የትግራይ ተወላጆችን አስፍረዋል።
ዛሬ የሁመራ ከተማ ብዙ የተለያዩ ኢትዮጵያውያን እንዳላኖረች 99.99% የትግራይ ተወላጅ ብቻ መዲና ሁናለች። ጥቂት መሄጃ ያጡ የወልቃይት ጠገዴ ተወልጆች ከሁመራ ከተማ 25 ኪሎሜትር ወጥተው ለብቻ እንዲሰፍሩ ተደርጓል (segregation )።

ለ) በብዙ ሺ የሚቆጠሩ የወልቃይት ጠገዴ ሴቶች አስገድዶ በመድፈር(rape)፤ ከትግራይ ተወላጆች እንዲወልዱ ተደርጓል፡ ከሁሉም በላይ የሚገርመው ነገር በኢትዮጵያ ታሪክ ታይቶና ተሰምቶ በማያውቅ መልኩ የወልቃይት ሴት የወር አበባዋ ስትጀምርና ስትጨርስ በወያኔ የጤና ጣቢያዎች እንድታመለክት በማስገደድ ለእርግዝናዋ አመቻችተዋል።

የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጭ ግንባር ግፍ በዚህ አላበቃም፤ በጉልበት ለነጠቁትን መሬትና ለሠሩት ወንጀል ነገ ጠያቂ እንዳይኖር ለማድረግ በስደት ሕይወታቸውን ያተረፉ የወልቃይትና ጠገዴ ሰዎችን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከማሳደን ከማጥፋትና ከማፈን ተቆጥባ አታውቅም።
በተለይ ከሱዳን መንግሥት ጋር በሚያደርጓቸው ሚስጥራዊ አሁን በገሀድ እየታየ ያለው "የኢትዮጵያ ለም መሬት ለፀጥታ" land for security" ስምምነት፤ ብዙ የወልቃይት ጠገዴ ተወላጆች ታፍነው እንዲጠፉ፤ ታስረው ለወያኔ እንዲሰጡ እየተደረገ ነው። ባለፈው መስከረም 30, 2000 ዓ.ም የሱዳን መንግስት የአለም ሕብረተሰብ ጩኸት ከመጤፍ ሳይቆጥር የእለት ኑሯቸውን ለማሸነፍ ሌት ተቀን ሲባዝኑ ለኖሩት 15 (አስራ አምስት) ኢትዮጵያውያን በሰንሰለት አሥሮ ለወያኔ አስረከበ። በወያኔ ጠቋሚነት በዚች ሰዓትም በሱዳን ፀጥታ ኅይሎች በመታደን ላይ ያሉ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ወገኖች ብዙዎች ናቸው።
ከሱዳን ባሻገር ወያኔ ወደ ሃገረ አሜሪካ በመዝዝ ተሰዶ ነገር ግን ለወገን አለኝታ የሆነውን፤ ኢትዮጵያ ውስጥ እየተካሄደ ያለውን ጸረ ወያኔ ትግል በሁለንትናዊ መልኩ የሚረዳውን፤ ወያኔ ተመጽዋች ያደረገችውን ሕዝብ በኢኮኖሚ በሞራል በመሳሰሉት ድጋፍ በመስጠት ላይ ያለውን የወልቃይት ጠገዴ ተወላጅ ኢትዮጵያዊ ለማታለል፤ ለመከፋፈል፤ ቢቻልም የወያኔ ጠባብና ከፋፋይ ፖለቲካ ተቀብሎና አምኖ እዲጓዝ ለማድረግ ጥቂት ሕሊናቸውን ከሸጡ ያካባቢው ተወላጅ ነን ተብየዎች ጋር በመመሻጠር ወያኔ በትውልድ ወልቃይት የሆኑት አቶ ፈረደ የሸወንድምና አቶ ፀጋይ አስማማው የሚባሉ ከሃዲ ባለስልጣኖቿ በነሐሴ ወር መላኳ ይታወቃል።
ባለስጣኖቹ "በልማት ስም" የጠልፎ መጣል ዘመቻቸውን ለማካሄድ ኮለምበስ ከተማ ስብሰባ መጥራታቸው ይታወሳል። ከጀግና አብራክ የወጣው የወልቃይት ጠገዴ ተወላጅ የወያኔ ባለስልጣናትና የወገንና የሃገር ፍቅር የሌላቸው ምንደኛ ግብረ አበሮቻቸው ከጠሩት ስብሰባ በመገኘትና ፊት ለፊት በመጋፈጥ የመጡበት አላማ እንዳይሳካ፣ ተልእኮአቸውም እንዳይሰምር በማድረግ ቅጥረኞችም ሆኑ ሆድ አደሮች አፍረው እንዲሄዱ አድርጓል። በነሐሴ18, 2007 ዓ/ም የተካሄደውን ስብሰባ አስመልክቶ የወጣው የተቃውሞ ያቋም መግለጫ ህያው ምስክር ነው። በዚህ የጠልፎ መጣል የተታለሉ ከአሥር የማይበልጡ ወገኖች በነዚህ ሕሊናቸው በሸጡና ለወያኔ መሰሪ አላማ በቆሙ ግለሰቦች ተታለው የአብዛኛው ሐገር ወዳድ ምክር ሳይሰሙ የርሻ መሬት ሁመራ እንደሚሰጣቸው ቃል ተገብቶላቸው ያለ የሌለ ገንዘባቸው አሟጠው በእርሻ መሣሪያዎች ላይ አውለው የተጠየቁትን ሁሉ አሟልተው ወደ ሁመራ ሄዱ።
እነዚህ ለማረስ ወደ ሁመራ የሄዱትን የወልቃይት ጠገዴ ተወላጆች መምጣትን አስመልክቶ የሁመራ ከተማ ኗሪዎች (99.9% የትግራይ ሰዎች) በተደጋጋሚ የሕዝብ ስብሰባዎችን በማካሄድ በየካቲት 14 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ስብሰባቸው ላይ "ደማችን አፍሰን አጥንታችንን ከስክሰን የያዝነውን መሬት ተመልሰን

ለወልቃይት ጠገዴ ሰው ፊፅሞ አንሰጥም…" የሚል ቁርጥ ውሳኔ አስተላለፉ። ተታለው የሄዱት ወገኖች ኪሳራቸውን ተጎናፅፈው ቁጭ ብለዋል።
ውድ ኢትዮጵያውያን ወገኖች እዚህ ላይ ልብ እንድትሉልን የምንፈልገው በመግቢያችን ላይ እንደገለፅነው <u>የትግራይ ሕዝብ</u> ባለውለታው በሆነው በዚህ አገርና ወገን ወዳድ ጀግና የወልቃይት ጠገዴ ተወላጅ ኢትዮጵያዊ ላይ ወያኔ የፈፀመቻቸውን፤
ሀ) ወገንን የማጥፋት ዘመቻ (ethnic cleansing) ምንም አይነት ያዘኔታ ምልክት ሳያሳይ መቅረቱ፤
ለ) የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ ከባእድ ወራሪ ተከላክሎ የፀሐይ ቃጠሎ የወባና የመሳሰሉትን በሽታዎች ተቋቁሞ ያለማውን መሬት ያፈራውን ቤት ንብረት ወርሶ፤ ሴት ልጆቹን አስገድዶ ደፍሮና ደቅሎ ይባስ ብሎም ተታለው ሊያርሱ በሄዱት ወገኖች ላይ ወያኔ ዝቶና አፋጠ ወዘተ... እንዴት ነው የትግራይ ሕዝብ ዝምታ? ባለውለታ ያሰኛል! ከወያኔስ በምን ይለያል! ፍረዱን!!!
ውድ ወገኖች ልጅ ለእናት ይጮሀል ሆኖብን እንጂ የወልቃይት ጠገዴችግር ሊፈታ የሚችለው የእናት ኢትዮጵያ ችግር ሲፈታ ብቻ እንደሆነ ግልፅ ነው፡ ታዲያ ለዚህም ነው የነፃነት ትግላችን ያለፋታ መቀጠል ያለበት፡ ለዚህም ነው የወገን ጎራ ልዩነቱን በአስቸኳይ አጥብቦ "ሀገር የማዳን" እንቅስቃሴ በአስቸኳይ መካሄድ ያለበት የምንለው።
ባለፈው ወር ወያኔ የኢትዮጵያ ለም መሬት ለሱዳን አሳልፎ በመስጠቱ የታች አርማጭሆ ሕዝብ በቁጣ ተነስቶ የሱዳንና የካሃዲው ወያኔ ወኪሎች ያስቀመጧቸው የደምበር ምልክቶች በመነቃቀል ድርጊቱ ሁለተኛ እንዳይደገም ዘብ ቆሞ እያደረ መሆኑ ከስፍራው ከሚገኙት ወገኖች ለማወቅ ተችሏል። ይህ በዚህ እንዳለ April 21-2008 ( ሚያዝይ 13) ወራሪው የሱዳን ጦር የኢትዮጵያን ዳር ደምበር ጥሶ በመግባት የአፄ ቴዎድሮስን ( መይሳው ካሳ) የትውልድ ሃገር የሆነችውን የቋራ ተራሮችን በመቆጣጠር ከ24 በላይ የኢትዮጵያውያን የእርሻ ጣቢያዎችን በማቃጠልና ብዙ ንብረቶችን በመዝረፍ ጥፋት ማድረሱንና 34 ኢትዮጵያውያን አርሶ አደሮች አስሮ መውሰዱ ተረጋግጧል።

ውድ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን የወያኔ ቡድን ገና ኢትዮጵያን በተቆጣጠረ ማግሥት ኤርትራን ያስቀረሰ፤ እልፍ አእላፍ ሂወት የጠፈበትን የባድመን መሬት አልጀርስ ድረስ ሮጦ ሂዶ ፈረሞ የሰጠው ከሃዲ ቡድን፤ ዛሬም ለም መሬታችንን ለሱዳን በመስጠት ላይ ይገኛል። ይህንን እኩይ ድርጊት በሁለንተናዊ መልኩ ለመመከት መላው ኢትዮጵያዊ ነገ ዛሬ ሳይል ልዮነቱን አጥቦ ሃገሩንና ወገኑን ለማዳን አብሮ እንዲቆም በዚህ አጋጣሚ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

ኢትዮጵያ በልጆቿ ትብብርና ትግል ነፃ ተወጣለች!!

ከወልቃይት ጠገዴ ተወላጅ ኢትዮጵያውያን በሰሜን አሜሪካ።